# ደንብ

## ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ሠነዶች፦
ኃላፊነት ያለው ቢሮ፦ Deputy Superintendent of Schoolsየት/ቤቶች ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

## ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዞች

**I.** ዓላማ

ተማሪዎች የድንገተኛ ጊዜ የህክምና አገልግሎቶች (EMS) "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዞች" ሲኖራቸው የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ለማቅረብ።

**II.** የቀድሞ መነሻ

MCPS ህይወትን-አደጋ ላይ የሚጥሉ የጤና ችግሮች ያሉባቸው ተማሪዎች ከትክክለኛ/ተቀባይነት ያለው የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዞች" ጋር ት/ቤት መማር እንደሚችሉ ያውቃል። ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን የጤና እንክብካቤ እርምጃዎች በሚመለከት ውሳኔዎችን የመስጠት መብት አላቸው። ነገር ግን፣ የት/ቤት አካባቢ ለሁሉም ተማሪዎች ደህንነት ሲባል ስርዓቱን የጠበቀ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ከስጋቶች ነፃ መሆን አለበት። በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የተማሪ ህይወት ማለፍ ለተማሪዎች እንዲሁም ለሰራተኞች አሰቃቂ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም፣ በት/ቤት አካባቢ ውስጥ የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ትግበራ በግል/በተናጠል መመዘን አለበት እና ከዚህ በታች የተገለፁትን የአሰራር ቅደም ተከተሎች በመጠቀም እያንዳንዱ ጉዳይ በተናጠል መፍትሄ ሊያገኝ ይገባል።

**III.** ትርጉሞች

A. የ *EMS* "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ *(DNR)* ትዕዛዝ" ማለት በሜሪላንድ የድንገተኛ ጊዜ ህክምና አገልግሎቶች "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ቅፅ ላይ በህክምና ባለሙያ የተፃፈ ትዕዛዝ ሲሆን፣ በግለሰብ ላይ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል የህክምና ክስተት ሲፈጠር የመተንፈሻ አካላትን ማስነሳት/ማንቃት (CPR) እና ሌላ አደገኛ የህክምና አሰራር ሂደቶች መተግበር/መደረግ እንደሌለባቸው የሚገልፅ ነው።

B. የጤና አገልግሎቶች ባለሙያዎች ማለት ሀኪሞች፣ የተመሰከረላቸው/እውቅና ያላቸው ነርስ የህክምና ባለሙያዎች፣ ወይም የተመዘገቡ ነርሶች ሆነው ከልጆች እና ከወላጆች ጋር በት/ቤት የጤና ፕሮግራሞች ላይ የስራ ልምድ እና ወይም ልዩ ስልጠና የወደዱ ናቸው።

C. *EMS* ህመምን የመቀነስ/የማረጋጋት *(Palliative)* እንክብካቤ/ ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ፕሮቶኮሎች ማለትበግለሰብ ላይ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል የህክምና ክስተት ሲፈጠር መረጋጋት እና ምቾትን ለማቅረብ የሚያገለግሉ ከሜሪላንድ የድንገተኛ ጊዜ ህክምና አገልግሎቶች ስርዓቶች ውስጥ መደበኛ የጤና እንክብካቤ አሰራር ቅደም ተከተሎች ናቸው። የአሰራር መመሪያዎቹ የመተንፈሻ አካላትን ማስነሳት/ማንቃት

(CPR) እና ሌላ አደገኛ የህክምና አሰራር ሂደቶችን አያካትቱም። ለግለሰብ እንደ ኦክስጅን የመስጠት አይነት የማረጋጋት እርምጃዎች ይቀርባሉ።

D. የ የድንገተኛ ጊዜ የህክምና አገልግሎቶች "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ቅፅ ማለት መደበኛ/ኦፊሻላዊ፣ ቁጥር ያለው ቅፅ ሆኖ ከቁጥር የተሰጠው የግል መታወቂያ አምባር/እጅ ላይ የሚደረግ ጋር ተመሳሳይ/አብሮ የሆነ ሲሆን ትክክለኛ DNR ትዕዛዝ ያለው ግለሰብን ለመለየት የሚጠቅም ነው። 911 ከተደወለ እና ዋነኛው የትዕዛዝ ቅፅ ወይም አምባር/እጅ ላይ የሚደረግ ከታየ፣ በድንገተኛ ጊዜ ሰራተኛ የህይወት ድጋፍ አይሰጥም። የማረጋጋት እርምጃዎች ይቀርባሉ።

IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. የሜሪላንድ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ያላቸው ተብለው በተለዩ የሁሉም ተማሪዎች ወላጆች የት/ቤት ጤና ነርስ ማሳወቂያ ይደርሰዋል/ሳታል። የት/ቤት ጤና ነርስ ተግባርም፦

1. ለዳይሬክተር ማሳወቅ እና፣ አስፈላጊ ከሆነ፣ ወላጅ/አሳዳጊ የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ" (DNR) እና የህክና ትዕዛዝ ቅፅ እንዲያገኙ ማገዝ።

   ሁሉም ተማሪዎች ትክክለኛ/ተቀባይነት ያለው የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ" (DNR) እና የህክምና ትዕዛዝ ቅፅ እና አምባር/እጅ ላይ የሚደረግ እንዳላቸው ማረጋገጥ።

   የተፈረመበትን ትዕዛዝ ማግኘት የወላጅ/አሳዳጊ ሀላፊነት ነው። ትክክለኛ ማንነት መለየትን ለማረጋገጥ የእጅ አምባሩ/እጅ ላይ የሚደረገው ሁልጊዜም በተማሪ መደረግ አለበት። የእጅ አምባሩ ት/ቤት ለተፈጠረው ድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪዎች/የመጡት የድንገተኛ ጊዜ ህክምና ሰራተኞች ወዲያውኑ እንዲያዩት ይደረጋል።

2. በተማሪ የጤና ሰነድ/ፎልደር ውስጥ የተፈረመበት EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ቅፅ ግልባጭ መቀመጥ አለበት። በቅፁ ላይ ያለው ቁጥር እና በእጅ አምባሩ ላይ ያለው ቁጥር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

3. የግል የጤና እንክብካቤ ዕቅድ እስካሁን ድረስ ከሌለ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ተገናኙ እና አዘጋጁ። የጤና እንክብካቤ እቅድን በሚመለከት የህክምና ባለሙያን ያማክሩ።

4. "ማወቅ በሚገባ ልክ" መሰረት የት/ቤት እና የመጓጓዥ ሰራተኞችን አሰልጥኑ።

   ስልጠና ማካተት ያለበትም የተማሪ ጤና ሁኔታ እና የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅድ ዝርዝሮች ላይ መረጃ፣ የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ፣" የእጅ አምባር፣ የ EMS ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ፕሮቶኮል፣ እና ማንኛውም ሌላ ተዛማጅ ጉዳዮችን ነው።

5. በት/ቤት ሰአታት ወቅት ለግለሰብ የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት ትምህርት እና ማማከርን በሚመለከት የተማሪ ማህበረሰብ ፍላጎቶችን በሚመለከት የነርስ ግምገማ አድርጉ።

B. የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" የመጨረሻ መቀበልን አስቀድሞ፣ ዳይሬክተሩ የተለያዩ በተማሪ ጤና እንክብካቤ ላይ የሚጠበቁ ነገሮችን ለማብራራት ከወላጅ/አሳዳጊ፣ የት/ቤት ጤና ነርስ፣ ከመዳጓዣ ቢሮ ተወካይ (ለዚህ የሚያገለግል ከሆነ)፣ ከሀኪም (ከተቻለ)፣ ከአካባቢ የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪዎች፣ እና ከተማሪ ጋር፣ ተገቢ ከሆነ፣ ቢያንስ አንድ የዕቅድ ስብሰባ ያካሂዳሉ።

C. የ EMS ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ የህክምና ፕሮቶኮል የሚከተሉት ካልተሟሉ ተፈፃሚ አይሆንም፦

1. ትምህርት ቤቱ የህክምና አደጋ በሚከሰትበት ወቅት ተማሪው/ዋ CPR መውሰድ እንደሌለባቸው የሚገልፅ ተቀባይነት ያለው/ትክክለኛ የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ቅፅ በሜሪላንድ ውስጥ ፈቃድ ካለው ሀኪም መቀበል አለበት። ትእዛዙ መቀመጥ ያለበት የሜሪላንድ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ቅፅ ላይ ነው።

2. ወላጅ/አሳዳጊ ከ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ጋር መስማማት በፅሁፍ በመግለፅ ለት/ቤት ማሳወቅ አለባቸው።

3. የት/ቤት ጤና ነርስ የ EMS "ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ" ምን እንደሚያካትት ማብራሪያ ሊደርሰው/ሳት ይገባል፣ ይሄም የተፈቀዱ እና የተከለከሉ የሆኑትን የተለዩ አሰራር ሂደቶች ላይ ማብራሪያን ጨምሮ ነው።

4. ተገቢ የሆነ ስልጠና፣ "ማወቅ በሚገባ ልክ" መሰረት በትምህርት ቤት ነርስ ተካሂዷል፣ ይሄም የተፈቀዱ እና የተከለከሉ የሆኑትን የተለዩ ቅደም ተከተሎችን ማብራሪያን ጨምሮ ነው።

5. መደበኛ የፅሁፍ የጤና እንክብካቤ ዕቅድ በተመደበ/ች የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች ባለሙያ ተዘጋጅቷል፣ ከሀኪም እና ከወላጅ/አሳዳጊ ግብዓቶችን በማካተት፣ እና በወላጅ/አሳዳጊ፣ በሀኪም፣ በት/ቤት አስተዳደር እና ተገቢ ከሆነ በተማሪ ተፈርሞበታል።

D. የህክምና አደጋ

የተፈረመበት የግል ዕቅድ በማይኖርበት ወቅት የህክምና አደጋ ያጋጠማቸው ሁሉም ተማሪዎች መደበኛ እርምጃዎችን ለመጀመሪያ እርዳታ እና CPR የሚወስዱ ይሆናል። የቀዳሚ/መጀመሪያ ምላሽ ሰጪዎች ድርጊቶች የሚመሩ የሚሆነው በት/ቤት ጤና የመጀመሪያ እርዳታ መመሪያ/ማንዋል ላይ በተቀመጡ ቅደም ተከተሎች፣ እና በመጀመሪያ እርዳታ እና CPR ምስክር ወረቀት ማግኛ ኮርሶች/ትምህርቶች ጊዜ በተወሰዱ ስልጠናዎች መሰረት ነው።

E. ሚስጥራዊነት

የተማሪ ሚስጥራዊነት መጠበቅ አለበት። ለት/ቤት ሰራተኛ እና ተማሪዎች የተማሪ የህክምና ሁኔታን ማሳወቅ በሚመለከት ወላጅ/አሳዳጊ ጋር ምክክር ይደረጋል። ዳይሬክተሩ/ሯ፣ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር በመተባበር፣ የተማሪን ጤና ሁኔታ በሚመለከት የትኞቹ የት/ቤት ሰራተኞች ሊነገራቸው እንደሚገባ ይወስናሉ።

F. የዕቅድ ግምገማ

የ EMS “ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዞች” እና ተዛማጅ የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅዶች እንደ አስፈላጊነቱ፣ እና ቢያንስ በየአመቱ፣ የመቀጠሉን ተገቢነት ለመወሰን መገምገም አለባቸው። በግምገማው ላይ ወላጅ/አሳዳጊ መሳተፍ ይኖርባቸዋል እና ትእዛዙን መፈረም አለባቸው። በሁሉም ጉዳዮች ውስጥ ለሀኪም ማሳወቅ ይገባል። በተማሪ ጤና መዝገብ/ሬከርድ ውስጥ ግምገማ መካተት አለበት። ቢያንስ በየአመቱ የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅድ ላይ ወላጅ/አሳዳጊ መፈረም አለባቸው።

G. የትዕዛዝ መሰረዝ

የ EMS “ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ” ከተሰረዘ/ከቆመ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤት ዳይሬክተር በፅሁፍ ማሳወቅ አለባቸው። ዳይሬክተሩም/ሯም ወዲያውኑ ለት/ቤት ጤና ነርስ ያሳውቃል/ታሳውቃለ፣ በነርስም “ተቋርጧል” ተብሎ በቀይ የ EMS “ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ” ላይ ይፃፍበታል። የ EMS “ለማስነሳት/ለማንቃት እንዳትሞክሩ ትዕዛዝ” መቋረጡን ተገቢ ለሆኑ የት/ቤት ሰራተኞች ማሳወቅ የዳይሬክተር እና የት/ቤት ጤና ነርስ የጋራ ሀላፊነት ነው። ትእዛዙ ላይ የተደረገውን ለውጥ እና የተማሪን አሁን ላይ ያሉ ፍላጎቶች በሚያንፀባርቅ መልኩ የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅድ ላይ በት/ቤት ጤና ነርስ ማሻሻያ ይደረጋል።

ስለ ደንቡ ታሪክ፦ አዲስ ደንብ፣ ጁላይ 23፣ 1997፤ ኖቬምበር 19፣ 2007 የተሻሻለ።